ማስረጃን ፍለጋ

ስሜነህ

በትጥግ ትግሉ ወቅት የተደረገውን ጨምሮ ኢሕአዴግን ለ3ኛ ጊዜ የመታደስ እንቅስቃሴ ውስጥ ካስገቡት መሠረታዊ ጉዳዮች መካከል የመንግሥት ሥልጣንን የግል ጥቅም ማስከበሪያና የኑሮ መሠረት የማድረግ ዝንባሌ እንደወረርሽኝ መባዛቱ የመጀመሪያውና ዋነኛው ነው። ድርጅታዊ ሃላፊነትን ወደመንግስታዊ ስልጣን መወጣጫ ዋና መንገድ ተደርጎ መወሰዱም ያፈጠጠው ከዚሁ ከኪራይ ሰብሳቢነት መንሰራፋት ጋር ተያይዞ መሆኑ በየመድረኩ ላይ የተደረጉ ግምገማዎች ሁሉ ያረጋገጡት ጉዳይ ነው። የመንግሥት ሥልጣንን ለበጎ ዓላማ መጠቀም እየቀረ፣ በዝርፊያ ራስን ለመጥቀም ሲውል የድርጅቱንም ሆነ የሚመራውን መንግሥት ህልውና አደገኛ ሁኔታ ውስጥ መክተቱን ኢሕአዴግ መገምገሙን ተከትሎ በየደረጃው ጥልቀት ያለው ተሃድሶ እየተደረገ መሆኑን መንግስት አስታውቋል፡፡ በመንግሥት ውስጥም ሆነ ከመንግሥት ውጪ ባሉ ኃይሎች በነጠላም ሆነ በጥምረት ሲፈጸም ለኖረው ቅጥ ያጣ ሙስና መንግስትና ገዢው ፓርቲ ራሳቸውን የመጀመሪያ ተጠያቂ አድርገው ነው ወደ ተሃድሶው የገቡት።

ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ከጋዜጠኞች ጋር ባደረጉት ቆይታ፣ በሙስናና በኪራይ ሰብሳቢነት ላይ በተሳተፉ አመራሮች ላይ መንግሥታቸው እየወሰደ ያለውን ዕርምጃ አጠንክሮ ይቀጥላል ማለታቸው፤ በዚህ እንቅስቃሴ የሙስና ችግር አለባቸው ተብለው ጥቆማ በሚቀርብባቸው አመራሮች ላይ የተጠናከረ ምርመራ እንደሚካሄድ፣ ማስረጃ እስከቀረበ ድረስም መንግሥት ምሕረት እንደሌለው ገልጸዋል፡፡ በከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት ላይ ለምን ዕርምጃ አይወሰድም? ተብለው ለተጠየቁትም፣ በማስረጃ እስካልተረጋገጠ ድረስ ምንም ማድረግ እንደማይቻል፣ ነገር ግን ማስረጃ ከመጣ መንግሥት አይምርም ማለታቸው አነጋጋሪ እንደሆነ ቀጥሏል፡፡

. . . ህንፃ ያላረፈበት ባዶ መሬት ህንፃ እንዳለው አስመስሎ እንዲሸጥ ማድረግ፣ ከሻጭና ከገዥ ጋር በመመሳጠር በዝቅተኛ ዋጋ እንደተሸጠ አድርጎ ውል ማጽደቅ፣ ፋይሎችን ሆን ብሎ መደበቅ እና ሳይት ፕላን አዘጋጅቶ ለፕላን ማሰሪያ እና መደራደሪያ ማቅረብ፣ የጨረታው መመሪያ በሚያዘው መሰረት ሁሉንም መረጃዎች ሳያካትቱ ወደ ጨረታ ማውጣት፣ ወደ ጨረታ የሚወጣ መሬት ከይገባኛል ነፃ ሳይሆን በችኮላ ማውጣት፣ ከጨረታ በኋላ ከህግና አሰራር ውጭ ተመሳሳይ ስም በማለት ተለዋጭ መሬት መስጠት በዚህም የተነሳ ድሃው እየተጉላላ መሆኑን በጥናቴ አረጋግጫለሁ ያለን መንግስት እንደገና ማስረጃ የሚፈልገው ከወዴት ነው? በሁሉም ከተሞች እንደተነሳው በመጀመሪያ ለባለሙያውና ለአመራሩ በቤተሰብ፣ በአገር ልጅነትና በጓደኝነት አግባብ ያልሆነ ትስስር ለመፍጠር ይሰራል፣ ያለ ገንዘብ /ጉቦ/ የሚፈፀም ነገር የለም ብሎ የመደምደምና፣ በባለሃብቶቹ በኩል ደግሞ አለማልማትና መሬት አጥሮ ማስቀመጥ እንዲሁም በስታንዳርዶች በትክክል ስለማይሰሩ በጉቦ እንዲፈጸምላቸው ወይም እንዳይጠየቁ ሲሉ ጉቦ የመስጠት ሁኔታ እንደሚታይ እና ይህ ዝንባሌ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየበረታ መምጣቱንም በጥናቱ ይፋ ያደረገ መንግስት በእርግጥም ማስረጃ እየፈለኩ ነው ቢለን የሚያነጋግር እና ተሃድሶውንም አደጋ ላይ እንዳይጥለው የሚያሰጋ ነው፡፡

ሌላው የኪራይ ሰብሳቢነት ችግር በመሬት ዙሪያ የሚሰራ አመራርና ሰራተኛ የባለሃብት እና የደላላ ጥገኛ መሆን ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ባለሀብት 70ሺ ብር በማውጣት የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ የአዳማ አመራሩና ሰራተኞች ወደ ትግራይና ደቡብ ክልሎች መላካቸው ባለፈው አመት የፖሊሲ ጥናት ማእከል ባደረገው የጥናት ሰነድ ላይ ተገልጿል፡፡ በዚህም ምክንያት የፈለጉትን ያስወስናሉ፤ ጣልቃ በመግባት ሰራተኛ እንዲባረር ያስደርጋሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ የአዳማ ማዘጋጃ ቤት ሰራተኛ ከባለሃብቱ ጋር አለመግባባት በመፈጠሩና እንዲባረር መደረጉም ጭምር፡፡ ስለሆነም በዚህ ተሃድሶ በአዳማ ከተማ ላይ የተደረገው ጥልቅ ተሃድሶ ይህንን ጥያቄም በሚመልስ ደረጃ ካልሆነ ህዝቡ እምነት ያጣል።

ሌላው የፌዴራልና የክልል ከፍተኛ የፖለቲካ አመራሩ በመሬት ላይ ከፍተኛ ጣልቃ ገብነት መኖር ነው፡፡ ለምሳሌ በሰበታ አንዳንድ የፌዴራል ከፍተኛ አመራሮች ስልጣንን ያለአግባብ በመጠቀም በተለያየ ጊዜ በመሬት ሃላፊዎች ላይ ጫና እንደሚያሳድሩ፤ በከተማው ውስጥ የሚገኙ የቀበሌ አመራሮችና የድርጅት ሃላፊዎች በመሬት ስራ ላይ ጊዜያቸውን እንደሚያሳልፉም በጥናቱ ተብራርቶ ተገልጿል፡፡ በዚህ ጉዳይ እጃቸው ያለባቸው ከፌደራል እስከ ከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ የኦሮሚያ ባለስልጣናት ላይ ህዝቡ ከዚህ ተሃድሶ አንዳች ነገር እየጠበቀ በሚገኝበት ሰአት ላይ ማስረጃ ፍለጋው ግራ ቢያጋባን እና መነጋገሪያዎችን ቢሆን ሊገርም አይገባም።

በተመሳሳይ መልኩ በደቡብ የጥናቱ ግኝቱ እንደሚያሳየው የኪራይ ሰብሳቢነት ተግባርና አመለካከት በሁሉም ጥናት የተደረገባቸው ከተሞች መስተዋሉ በጥናቱ ተመልክቷል ፡፡ ለምሳሌ በዲላ የሃሮ ወላቡ ክፍለ ከተማ ህገ-ወጥ ቤቶች በማፍረስ ሂደት የራስ እና የዘመድ ቤተሰብ ህገወጥ ቤቶች እየመረጡ ሳያፈርሱ ማለፍ እና እንዳይጠየቁ የማድረግ ተግባራት፤ ከዚህም በተጨማሪ በህገ-ወጥ ይዞታ ለያዘው ዘመድ በቶሎ የይዞታ ማረጋገጫ እንዲሰጥ ማድረግ፤ ከዚህ ሌላ አመራሩ ራሱ ህገወጥ ተግባር ላይ እንደሚሳተፍ የተመለከተ ሲሆን፤ ለምሳሌ በሐዋሳ ዳቶ አካባቢ አንዳንድ አመራሮች በህገወጥ ግንባታ በስፋት የተሳተፉበት ሲሆን በተለያዩ ጊዜያት ይህንን ድርጊት ለማጣራት የገቡ ባለሙያዎች ተሸማቀው ከመመለሳቸውም በላይ ምክንያት ተፈጥሮ በህግ እንዲጠየቁ የተደርጉ መሆናቸውንም በጥናት እንዳረጋገጠ የገለጸ መንግስት ሃዋሳ ላይ ዛሬም ማስረጃ ፍለጋ ላይ እንደሆነ ሲገልጽ በእርግጥም ግራ ቢያጋባን ሊደንቅ አይገባም፡፡

በሀዋሳና ዲላ ማዘጋጃ ቤቶች ከመዝገብ ቤት ጀምሮ ፋይል የመደበቅና ባለጉዳይ የማጉላላት ችግሮች ያሉ ቢሆንም አመራሩ እያየና እየሰማ እንዳልፈታውና ባለጉዳይን ማጉላላት፣ ማጭበርበር፣ ቶሎ ምላሽ አለመስጠትና ጉቦ መቀበል በዋነኛነት የሚታይ ግልፅ ችግር እንደሆነ፤ የሚወጡ የሊዝ ጨረታዎች አንድ ሰው ከአንድ ጨረታ በላይ ሰነዶችን እንዲገዛቸው ማድረግ እየተለመደ የመጣ ችግር እንደሆነም መታየቱ በጥናቱ ተገልጧል፡፡

ሌላው በዚህ ክልል የታየው የኪራይ ሰብሳቢነት መገላጫ ጠባብነት ነው፡፡ እንደ ጥናቱ ግኝት በአንዳንድ ደቡብ ዞኖች ባለሙያን ቀጥሮ ከማሰራት ይልቅ የራስ /የአካባቢ/ ባለሙያ ከሚማርበት ተመርቆ እስኪመጣ መጠበቅ አለ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በህገወጥ ግንባታ በማፍረስም ሂደት የጠባብነቱ አመለካከትና ተግባር እየታየ እንዳለና በዚህ ምክንያት ሁልጊዜ አመራሮች እና ባለሙያዎች ከህዝቡ ጋር የሚጋጩ መሆናቸው ታይቷል፡፡ አመራሩ የጠባብነት አመለካከትና ተግባር ተዋናይ በመሆኑ ለከተማው ዕድገትና ለመሬት ልማት ከፍተኛ እንቅፋት መሆኑን ነው ጥናቱ የሚያሳየው፡፡ ከጠባብነት አመለካከት የተነሳ ቅድሚያ የማግኘት መብት ያላቸውና በቦታው ሲሰሩ የነበሩትን ወደ ጎን በመተው ለሌሎች አሳልፈው መስጠት ሁሉ ስለመኖሩ በጥናቴ አረጋግጫለሁ የሚል መንግስት ዛሬም ማስረጃ ፍለጋ ላይ ነኝ ማለቱ ውሃ አያነሳም፡፡

በተለይ የከፋ የጠባብነት ችግር የታየው በወልቂጤ ከተማ ነው፡፡ በወልቂጤ ከተማ ከጊዜ ወደጊዜ  ህገወጥ ግንባታ እየተስፋፋ ቢሆንም አመራሩ የቀቤናና የጉራጌ ብሔር የሚለውን የጠባብነት ክፍፍል አስወግዶ እርምጃ እንደማይወስድ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም የጠባብነት ችግር በተለያየ ደረጃ በሃዋሳና በዲላም  እንደሚንጸባረቅ ጥናቱ ያሳያል፡፡ ያም ሆኖ ግን በዚህ ጥልቅ ተሃድሶ መንግስት በወልቂጤ ሃዋሳና ዲላ በስንቶቹ አመራሮች ላይ እርምጃ መውሰዱን አለመግለጹ ሳያንስ ማስረጃ እያፈላለኩኝ ነው ቢል የህዝቡን ጥያቄ መመለስን እና የተጀመረውን ልማት ማስቀጠልን አላማ ያደረገው ጥልቅ ተሃድሶ ውሃ እንዲበላው መፍቀድ ይሆናል። በመቀሌ ደግሞ ሁለት አመት የተፈረደበት እስረኛ ወጥቶ ከውጭ ሲንጎማለል ሰው በመግጨት እንደገና በተያዘ ደረጃ የተረጋገጠ የኪራይ ሰብሳቢነት አጀንዳ ውስጥ የተዘፈቁ አመራሮች ስለመኖራቸው በጥናቱ ያረጋገጠ መንግስት ማስረጃ በማጣቱ ዛሬም የክልሉ አመራሮች በሞቀው ወንበራቸው ላይ መገኘታቸው የሀድሶው ተረት ሆኖብናል።

በአዲስ አበባ የተደረገው ጥናት እንደሚያመለክተውም አመራሩ የቁርጠኝነት ችግር እንዳለበትና በኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከትና ተግባር የተዘፈቀ እንደሆነ፤ የመሬት ወረራና ሕገ-ወጥ ግንባታን እንዳላወቀ ማለፍ፤ በጥቅም ትስስር ምክንያት በህዝቡ የሚነሱ እሮሮዎችን ቸል ማለት፤ ሕዝብን ማስለቀስ፤ ማመናጭቅ፤ ማሸማቀቅ፤ ከሰራተኞች ጋር ተግባብቶ አለመስራት፤ አድሎአዊነት (የአንዱን የህገ-ወጥ ግንባታ አፍርሶ የሌላውን መተው) በሰፊው እንደሚስተዋል በጥናት ሰነዱ ተመልክቶ ሳለ የከተማው አስተዳደር የካቢኔ አባላት ላይ እንኳንስ እርምጃ ሊወሰድ ከወንበራቸውም ፍንክች ሳይሉ ማስረጃ እየተፈለገባቸው ነው ስንባል አንገት ያስደፋናል።

ባለጉዳይን “በእጅህ ካልመጣህ አገልገሎት አታገኝም” ብለው ቁርጡን የሚናገሩም እንዳሉ በጥናቱ ተጠቅሷል፡፡ በተለይ በስም ዝውውር ላይ በፈጻሚዎች ደረጃ፤ መሃንዲሶች ደግሞ የወሰን ችካል ሲሰሩ፣ ኢንቬንቶሪ ሲወስዱ፣ የግንባታ ፍቃድ ሲሰጡና የስም ዝውውር ሲሰሩ ትልቅ የኪራይ ሰብሳቢነት ድርጊት ይፈጸማል፤ በተጨማሪም መሃንዲሶች የራሳቸውን የግል ስራ በመንግስት ስራ ሰዓት እና በመንግስት ማቴሪያል በመጠቀም እንደሚሰሩና በተለይ የፕላን ስምምነት ሥራን በተመለከተ ትልቅ የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጭ ስለሆነ ባለጉዳይ ይዞ የሚመጣውን ፕላን መሃንዲሶቹ ከሚያቋውቸው ሰዎች ውጪ ተሰርቶ ከመጣ ሰበብና እንከን በማፈላለግ እንደማያጸድቁላቸው/እንደሚያንገላቷቸው አመራሩም እያወቀ እርምጃ እንደማይወሰድ ወዘተርፈ በጥናቴ አረጋግጫለሁ የሚል መንግስት ዛሬም በሃገር ደረጃ ማስረጃ ያገኘሁባቸው ከ120 ያልዘለሉ ናቸው ሲለን እየተደረገ ያለው ጥልቅ ተሃድሶ ሳይሆን የሌላ ያስመስልበታልና መንግስታችን በቶሎ ወደቀልቡ እንዲመለስ እንሻለን፡፡

በአጠቃላይ፣ ሙስናም ይባል ኪራይ ሰብሳቢነት ወይም ኃላፊነትን በአግባቡ አለመወጣት ከሥርዓቱ በተጨማሪ የአገርም አደጋ ነው፡፡ ጥልቅ ተሃድሶው የሃገርን ህልውና በዘላቂነት ታሳቢ ካላደረገ አደጋ አለው፡፡ በመፈራራት ወይም በእከከኝ ልከክህ እሳቤ ለመቀጠል ማሰብም ሆነ፣ የሕዝቡን ጥያቄ ከተገቢው ጊዜ በላይ በማራዘም መልስ መንፈግ ውጤቱ ጥሩ አይሆንም፡፡ ከላይ በተመለከተው አግባብ በመልካም አስተዳደር ችግሮችና በሙስና ላይ ጥናት አካሂዶ አስገራሚ መረጃዎችን ማቅረብ የቻለውን የኢትዮጵያ የፖሊሲ ጥናት ማዕከል ኢንስቲትዩት ይዞ፣ ማስረጃ ፍለጋ ሌላ ቦታ መባዘን ለአገር ከቶም አይጠቅም፡፡ ለሃገርና ለሕዝብ ዘለቄታዊ ሰላምና መረጋጋት ሲባል ሕግ እንዲከበር አስፈላጊው ሁሉ መደረግ አለበት የዚህ ፅሁፍ የማጠቃለያ መልእክት ነው፡፡